የሰ/መ/ቁ. 47201

ጥቅምት 5 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካቾች**፡- 1. በላቸው አስፋው ቀረበ

2. ሙክታር አሕመድ ቀረበ

3. ወ/ሮ ዙሪያሽ ወ/አረጋይ ቀረበች

4. አተረፈ ማሞ ቀረበ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ መኪያ አወል ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በሰበር ችሎቱ ሊመረመር በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ የይርጋ መቃወሚያን በተመለከተ የተሰጠውን ውሳኔ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ጉዳዩ ያለአግባብ የተያዘው ቤት ይለቀቅልኝ በማለት ተጠሪ ባቀረበችው ክስ መነሻነት የተካሄደውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ይለቀቅልኝ የምትለው ቤት አመልካቾች ይዘውት የሚገኝ ሲሆን፣በተጠሪ ክርክር እንደተገለጸው ባለንብረት የሆኑት ወ/ሮ አፀደ ገ/የሱስ የተባሉት ሴት ናቸው፡፡ ወ/ሮ አፀደ ገ/የሱስ ቤቱን አቶ ማንደፍሮ ቸርነት እና ወ/ሮ እልፍነሽ ቸርነት ለተባሉት ሰዎች በስጦታ ውል እንዳስተላለፉት፣በኋላም ወ/ሮ እልፍነሽ ቸርነት ድርሻቸውን በፈቃዳቸው ለአቶ ማንደፍሮ ቸርነት እንደተው፣አቶ ማንደፍሮ ቸርነት ደግሞ የተጠሪ አውራሽ እንደሆኑ በተጠሪ ክስ ተገልጾአል፡፡ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መልስ በየበኩላቸው ከአቶ ማንደፍሮ ቸርነት ጋር ባደረጉት የሺያጭ ውል ቤቱን መግዛታቸውን፣ በገዙት መጠን ቤቱን ይዘው ከ11 እና ከ13 ዓመት በላይ ሲጠቀሙ መቆየታቸውን፣ወ/ሮ አፀደ ገ/የሱስ ለአቶ ማንደፍሮ ቸርነት እና ለወ/ሮ እልፍነሽ ቸርነት አደረጉት የተባለው የስጦታ ውል በሕጉ አግባብ ፍፃሜ አላገኘም፤በዚህ አይነትም ከ21 ዓመት በላይ ቆይቶአል፣በመሆኑም ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል የሚሉትን ነጥቦች በማንሳት ተከራክረዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ክርክሩን የመረመረ ሲሆን፣በመጨረሻም አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ በማድረግ ቤቱን ለተጠሪ እንዲለቁ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣በአመልካቾች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል

በመጨረሻም ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረብዋ በዚህ ደረጃም ክርክር የተሰማ ሲሆን ፍ/ቤቱ አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ ይልቀቁ በማለት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካቾች ሰኔ 10 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በመቀጠልም ከግራ ቀኝ ወገኖች የቀረበውን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዚህ ሰበር ችሎት የሚመረመረው ጭብጥ አመልካቾች ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ተደርጐ ቤቱን ይልቀቁ የተባለው በአግባቡ ነው ወይ? የሚለው ጭብጥ ነው፡፡ አመልካቾች በተለይ ከ1 እስከ 3 ያሉት ቤቱን የያዙት ከአቶ ማንደፍሮ ቸርነት ጋር የሽያጭ ውል አድርገው በመግዛት እና የሺያጭ ዋጋውንም በመክፈል እንደሆነ በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ቢሆን የሽያጭ ውል አልተደረገም አላለም፡፡ የሺያጭ ውሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 የተመለከቱትን መስፈርቶች አያሟላም የሚል ምክንያት በመስጠት ነው ውልን በማስመልከት አመልካቾች ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ ያደረገው 4ኛ አመልካችም ቦታውን በቃል በተደረገው ስጦታ ተላልፎልኝ ቤቱን በራሴ ወጪ ሰርቻለሁ በማለት ቢከራከርም፣ስጦታው በጽሑፍ አልተደረገም በሚል ክርክሩ ተቀባይነት ሳያገኝ እንደቀረ ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቤቱ በአቶ ማንደፍሮ ቸርነት ስም አልተላለፈም (የስጦታ ውሉ ተፈፃሚ አልሆነም) የሚል ክርክር በአመልካቾች መነሳቱንና ተጠሪ ይህን በግልጽ አለማስተባበልዋን ተገንዝበናል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካቾች ቤቱን የያዙት ተጠሪ አውራሽ ነው የምትለው ሰው (አቶ ማንደፍሮ ቸርነት) በሕይወት በነበረበት ጊዜ ሆኖ ተጠሪ ክስ የመሰረተችው አመልካቾች ቤቱን ከያዙ ከ11 እና 13 ዓመታት በኋላ ነው፡፡ የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበትም አመልካቾች ቤቱን ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ እንጂ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ አገኘሁ ከምትልበት ጊዜ ጀምሮ አይደለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ተጠሪ የወራሽነት ማረጋገጫ ያወጣችበትን ወይም አቶ ማንደፍሮ ቸርነት የሞቱበትን ቀን መነሻ በማድረግ በይርጋ ረገድ የቀረበውን መቃወሚያ መወሰኑ ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአጠቃላይ የአመልካቾችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ በሕጉ አተረጓጐም ረገድ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲለቁ በማለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.31107 ሐምሌ 11 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይህን ውሳኔ በማጽናት በመ/ቁ. 43519 ሰኔ 15 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበችው ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ